


የተከበራችሁ ክቡራን እንግዶች !

የተከበራችሁ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ

የተከበራችሁ የመገናኛ ብዙሃን አባላት

የተከበራችሁ የመድረክ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

የተከበራችሁ የአንድነት ፓርቲ የብሔራዊ ም/ቤትና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

ክቡራትንና ክቡራን!

ጥሪአችንን አክብራችሁ ለዚህ ለዛሬው ታሪካዊ ዝግጅትና አናውንስሜንት በመገኘታችሁ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ በድጋሚ የላቀ ምሥጋና ለሁላችሁም ያቀርባል።

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መነሻ፤ የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤት፤ የተለያዩ የብሔረሰቦች ባህል፤ የሚገኙባት፤ ነፃነቷን በሕዝቧ ተጋድሎ የጠበቀች ታሪካዊ አገር ናት። ይህንን ደግሞ የነ ሉሲና አርደ፤ የአባ ጅፋር፣ የሐረር፤ የጎንደር፤ የላሊበላ፤ የ ነጋሽ፤ የአክሱም ሀውልት፤ ቤተ-መንግሥት፤ ቤተ-ኃይማኖትና ሌሎች የተለየዩ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ይመሰክራሉ።

ኢትዮጵያ የዘመናት አኩሪ ታሪክ ቢኖራትም ባለፉት ምዕተ-ዓመታት የመንግሥት አስተዳደር ሕዝባዊ ባለመሆኑና በእጅጉም እየተበላሸ በመሄዱ እነሆ አሁን ለአለንበት አሳፋሪና በጣም ዝቅተኛ ለሆነ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ልማት ደረጃ ተዳርገናል። ሌሎቹ የዓለም አገሮች በዴሞክራሲ እየበለፀጉና በልማት እየመጠቁ ወደ አዲሱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚሊኒየም ሲገቡ በኢትዮጵያ ግን ሕዝቡ በእርስ በርስ ጦርነት፣ በዴሞክራሲ እጦት፣ በጭቆና ብዛት በሥራ አጥነት፣ በረሀብ፣ በበሽታ እየማቀቀና እየሞተ ነው። በቅርብ ዓመታትም የሕዝብ ሥልጣን በኃይልና በይስሙላ ምርጫ የያዙት መንግሥትም ሆነ የተፈጠሩት ተቃዋሚ ፓርቲዎች የአደረጉት የፖለቲካ ትግልና የአመራር ሙከራ ሁኔታውን ለመለወጥ ጨርሶ አላስቻለም።

ደርግን በኃይል አሽንፎ ሥልጣን ላይ የወጣው ኢህአዴግ በነፃ ምርጫ የሚመሠረት ዴሞክራሲና ልማታዊ መንግሥት እውን አደርጋለሁ ቢልም ከፕሮፓጋንዳ አልፎ በተግባር ያመጣው ለውጥ የለም። በተገላቢጦሽ የፖለቲካ ምህዳሩን አዳፈኖ የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ መንግሥት እየሆነ ሕዝቡን አፋኝ አገዛዝ ሥርዓት፣ ለረሃብና ለድህነት ዳርጎታል።

የፖለቲካ ምህዳሩ ከተዘጋ በተለይ ደግሞ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ከሌሉ፣ የሰብአዊ መብት ከተጣሰ በአጠቃላይ የግለሰብና የዜጎች ነፃነት ከተገፈፈ በአገራችን በኢትዮጵያ ዘላቂ ልማት ጨርሶ አይመጣም። ድህነትና ረሀብም የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግሮች ሆነው ይቀጥላሉ።

በአገራችን እነዚህ መሠረታዊ የሕዝብና የልማት ችግሮች መንስኤአቸው የዴሞክራሲ የፍትሕ እጦት ነው። የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ እጦት ዴሞክራሲ በጠፋበትና ፍትሕ በሌለበት አገር ከችጋር የተላቀቀ ማህበረሰብና ዘለቂ የሆነ ልማት ማምጣት እንደማይቻል ታሪክና የብዙ አገሮች ተሞክሮ አስረድቷል። ዘላቂ ልማት በኢትዮጵያ ማስገኘት የሚቻለው ደግሞ በህግ የበላይነት ላይ የተመሠረተ እውነተኛ የዴሞክራሲ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር ሲኖር ብቻ እንደሆነ ማስገንዘብና ማሳወቅ እፈልጋለሁ።

አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በቂ ምግብ፣ በቂ ልብስ፣ በቂ መጠለያ፣ በቂ ጤንነት፣ በቂ ትምህርት፣ በቂ ንፁህ ውሀ፣ በቂ መብራት፣ በቂ ስልክ እንዲያው በአጭሩ በአስከፊ የኑሮ ሁኔታና የልማት ገጽታ ላይ በመገኘቱ የማያፍርና የማያዝን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይኖራል ብዬ አልገምትም።

የኢትዮጵያ አሳፋሪ የኑሮና የልማት ገጽታ ኢትዮጵያዊው ዜጋ ቀርቶ ሰው የሆነ ሁሉ የሚያሳስበው እና የሚያሳዝነው ጉዳይ ነው።

ክቡራትና ክቡራን!

እዚህ ላይ ትልቁ ጥያቄ ትልቅ ታሪክና ክብር የነበረው ህዝብ እንዴት አሁን በአሳፋሪና አሳዛኝ የሕይወት ታሪክ ላይ ሊገኝ ቻለ? የሚለው ነው። ብዙ ባለሙያዎች ሁኔታውን መርምረውታል። በአሁኑ ጊዜ መልሱ ብዙ ትንታኔ እና ምርምርም የሚጠይቅ አይደለም። ኢትዮጵያ ከትልቅ ባለታሪክነት ወደ አሳፋሪ የኑሮ እና ልማት ክስተት ልታሽቆለቁል የቻለችበት ዋንኛ ምክንያቶች የሠላምና የፍትሕ እጦት፤ የመልካም አስተዳደር እና የዴሞክራሲ ጥማት ናቸው። ኢትዮጵያ በታሪኳ የተራበችው ምግብ ብቻ ሳይሆን ሠላምና ፍትሕ እንዲሁም መልካም አስተዳደር ዴሞክራሲም ጭምር ነው። ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ከሌለ ልማትና እድገት በኢትዮጵያ ሊመጣ አይችልም።

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት የአገራችን የፖለቲካና የልማት ችግርና ምንም ያህል ውስብስብና አሳፋሪ ቢሆንም የአንድነት ፓርቲ ይህንን ሁኔታ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ በሰላማዊና ዴሞክሲያዊ ትግል እንደሚፈታውና እንደሚለውጠው ከወዲሁ አረጋግጣለሁ። ሕዝቡ ዝግጁ መሆኑን በተለያየ ጊዜ ገልፆታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ያሳየው የሚሊዮኖች መሰባሰብ እና በግንቦት 97 ምርጫ እለት በነቂስ ወጥቶ እስከ ምሽቱ 7፡00 ሰዓት ድረስ ወኪሉን በሠላማዊና ጨዋነት መምረጡ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምን ያህል ብቁና ዝግጁ መሆኑን በግልጽ ያስመሰከረበት ታሪካዊ ሐቅ ነው። ይህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴና አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ለወደፊት የፖለቲካና ልማት እድገት በር ከፋች ሆኖ ሊቀጥል ሲችል በገዢው ፓርቲ አምባገነንነትና በተቃዋሚ ፓርቲዎች አለመጠናከር ሊጨልም ችሏል። ስለዚህ የወቅቱ የኢትዮጵያ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ችግር፤ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትና የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ተጠናክሮ አለመገኘት ሲሆን አንድነት ይህንን ለመለወጥ አስፈላጊውን የተግባር እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።

የአንድነት ፓርቲ ነሐሴ 16 ቀን 2001 ዓም ሕጋዊ እውቅና ከአገኘ በኋላ በመላ አገሪቱ የአቋቋማቸው የፓርቲ ቢሮዎች 87 አካባቢ ይደርሳሉ፡፡ ቢሮ ሳይቋቋም ወደ 170 ለሚጠጉ የወረዳ የፓርቲ ኮሚቴዎች ተመሥርተዋል፡፡ ሕዝብዊ ስብሰባዎችን በአዲስ አበባ፤ በደብረማርቆስ፤ በአዳማ፤ በአዋሳ አካሂደናል፡፡  የአዳማው ስብሰባ፣  በገዢው ፓርቲ ቢቋረጥም፣ በፖለቲካ እድምታው በአገራችን እየተካሄደ ያለውን መጠነ ሰፊ የዴሞክራሲ መብቶች አፈና በግልጽ ለመላው ሕዝብና ለዓለም ሕብረተሰብ አሳይቷል፡፡ ከፍተኛ አመራሩ በመላ አገሪቱ የመስክ ጉብኝት በማድረግ አባላቱንና ሕዝቡን አነቃቅቷል፡፡ በገዢው ፓርቲ የተደረጉትን የፖለቲካ አፈና፤ እስራትና ወከባ ተቋቁሟል፡፡

በሰሜን አሜሪካ፤ በአውሮፓ፤ በአውስትራሊያ በደቡብ አፍሪካ በጠቅላላው ከ22 የሚበልጡ የአንድነት የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ተቋቁመው የፓርቲውን የዲፕሎማቲክና የማቴሪያል አቅም በከፍተኛ ደረጃ እያጠናከሩት ይገኛሉ፡፡ ለዚህም በሰሜን አሜሪካ ካናዳን ጨምሮ በአውሮፓ በአውስትራሊያ ለሚገኙት ትውልደ ኢትዮጵያውያን በዚህ አጋጣሚ ከፍተኛ ምስጋና  አንድነት ያቀርባል፡፡

በአገር ውስጥና በውጭ አገር መጠነ ሰፊ የሆነ የሕዝብ ግንኙነት በበራ ወረቀቶች፤ በሰሙናይ ሳምንታዊ ልሳንና በጽናት መጽሔት፤ በተለያዩ ወርክሾፖች፤ በበርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችና ቃለ-ምልልሶች ተካሂደዋል፡፡ በፓርቲው ዋና ጽ/ቤትና በቅርንጫፍ ቢሮዎች ሳምንታዊ የአባላት ስብሰባና ውይይት ተካሂዷል፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ ሥራና ሕዝባዊ መሠረት ያስደነገጠው ገዢው ፓርቲ ይች ባቄላ ከአደረች አትቆረጠምም የሚለውን ፈሊጥ በመጠቀም የፓርቲውን ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከሕግ አግባብ ውጭ የዛሬ 333 ቀን ታህሳስ 20/2001 ዓም አሠራት፡፡ ብርቱካንን በማሰሩ ብቻ አልረካም፡፡ ለብቻዋ በትንሽ ክፍል ከሰው ሳትገናኝ ለ170 ቀኖች ብቻዋን እንድትታሠር አድርጓል፡፡  በትግል አጋሮቿ፤ በዘመዶቿና በጓደኞቿ በአጠቃላይ በሚወዳት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለገደብ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 21 መሠረት እንድትጠየቅ ፍ/ቤት ሁለት ጊዜ ቢወስንም

መንግሥትና ማረሚያ በቱ ሊቀበለው አልቻለም፡፡ ሕገ መንግሥቱን እንደፈለገ የሚጥስ አካል በምን የሞራል ብቃትና የሕግ አግባብ ሌሎች እንደሚወንጅልና እንደሚያስር ግራ የሚያጋባ ገዳይ ነው፡፡

የዩኒኒቨርሲቲ ወይም የኮሌጅ ምሩቆች ሥራ ለማግኘት የኢህአዴግ አባል መሆን አለባቸው፡፡ በሥራህ ላይ ለመቆየት ወይም በችሎታ የሥራ እድገት ለማግኘት የኢህአዴግ አባልነት ፎርም በመሙላት ግዴታ እየሆነ ነው፡፡ ሥራ የማግኘት፣ በሥራ የመቆየትና በሥራ ማደግ የዜግነት መብት መሆኑ ቀርቶ በኢህአዴግ አባል የመሆን ግዴታ መተካቱ አጅግ አሳሳቢ የሆነ የሰብአዊና የዜግነት መብት ረገጣ ነው፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ፣ የዴሞክራሲና የኢኮኖሚ መብቶች መገደብ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠንክረው ሊታገሉባቸው የሚገቡ የፖለቲካ አጀንዳዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መሠረታዊ አገራዊና ሕዝባዊ ችግሮች በአንድ ፓርቲ ብቻ ሊፈቱ እንደማይችሉ አንድነት ያምናል፡፡ በዚህም እምነቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መደረክ በአጭሩ መድረክን በመቀላቀል የኢትዮጵያን ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጎራ አጠናክሩአል፡፡

አንድነት በመድረክ አማካይነት አዲስ የፖለቲካ ባህል (New Political Culture) እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በዚህም ኋላ ቀር የፖለቲካ አስተሳሰቦችን እያመከነው፡፡ እንደ አንድነት ያሉ የህብረ ብሔር ፓርቲዎች በብሔር ከተደራጁ ፓርቲዎች ጋር መሥራት አደገኛ ነው የሚሉትን በመድረክ አማካይነት ምንም ዓይነት አደጋ እንደሌለው አንድት በወሬ ሳይሆን በተግባር አሳይቷል፡፡ በአንድነት እምነት የህብረ-ብሔርና ብሔር ፓርቲዎች አብሮ መሥራት የኢትዮጵያን አንድነትና የሕዝቦቿን አብሮ በእኩልነት የማደግ ሂደት በዘለቄታውና በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚረጋገጥ ያበስራል፡፡

አንድነት የፓርቲዎችን የአደረጃጀት ልዩነትን ያከበራል፡፡ ልዩነት የኢትዮጵያውያኖች አንድ ውበት እንጂ ለአንድነታችን መዳከም ምክንያት ሊሆን እንደማይችል አንድነት በጽኑ ያምናል፡፡ በቅርቡ በብራስልስ የተመረጡት የአውሮፓ ህብረት ፕሬዚደንት የቤልጂየሙ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚስተር  በአውሮፓ መሪዎች ፊት የተናገሩትን በእንግሊዝኛ እጠቅሰዋልሁ፡ ፡ የአሉትም መሪ ቃል ''Our Unity is our strength our diversity is our wealth''

በአንድነት የፖለቲካ ባህል በህብረ ብሔራዊና እና በብሔራዊ ፓርቲዎች መካከል በዴሞክራሲያዊ መርህ እስከተመሩ ድረስ ምንም ዓይነት ተቃርኖ አይኖርም። በአንድነትና በሌሎች ሰባት ፓርቲዎች መስከረም 20 ቀን 2002 ዓም የተመሠረተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በማጠናከር ወደ ግንባርና ውህደትና ደረጃ በደረጃ እንዲሸጋገር አንድነት ተገቢ ሚናውን የሚጫወት መሆኑን በዛሬው ታሪካዊ ቀን አረጋግጥላችኂለሁ።

መድረክ ወደ ላቀ የትብብር ደረጃ እንዲደርስ የአባል ፓርቲዎች የወደፊት ዓለማ ሲሆን፣ የዚህ ራእይ ተካፋይ ከሚሆኑ ቃዋቂ ዜጎች መካከል ሁለት ሰዎች ጎልተው ይወጣሉ።

እነሱም፡-

1ኛ የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የተወካዮች ም/ቤት አባል፣ የቀድሞው የኢትዮጱያ ፌዴራላዊ ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ ፕሬዚደንትና የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ አባል የነበሩት፣

2ኛ የተከበሩ አቶ ስዬ አብርሃ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ መከላከያ ሚኒስትርና የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ አባል የነበሩት ናቸው።

ዶ/ር ነጋሶና አቶ ስዬ የመጀመሪያው የመድረክ አመራር አባላት ሲሆኑ፤ በአላቸውና በአካበቱት የፖለቲካ እውቀትና ብስለት ለመድረክ መጎልበትና ማደግ ከአንድ ፓርቲ ድርጅት ባለአነሰ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። በዚህም ሚናቸው የመድረኩ የፖለቲካ አርክቴክት ናቸው። በዛሬው ቀን አንድነትን ሲቀላቀሉ በሌላ በኩል የተቀላቀሉት መድረከን ጭምር ነው።

ዶ/ር ነጋሶና አቶ ስዬ በኢህአዴግ ውስጥ በነበራቸው የከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን እርከን የላቀና የተንደላቀቀ ህይወቶች በላይ የሆነ ሕይወት መኖር ይችሉ ነበር። ኖረውታል።

የዶ/ር ነጋሶ መኖሪያ ኢዮ-ቤልዩ ቤተ-መንግሥት ነበር። በሚሊዩን ብር በላይ በሚገዙ ዘመናዊ ኮብራ የቶዮታ መኪና በልዩ እንክብካቤ ታጅበው ሥራቸውንና ሕይወታቸውን ይመሩ ነበር። ይህን ዓይነቱ የሥልጣን ሹመት በተመሳሳይ ደረጃ የተመጣጠነ የህሌና ሹመት አላስገኘለቸውም። ነፃነት አጡበት 40 ዓመት ሙሉ የታገሉለት ዴሞክራሲና ፍትሕ ጠፋባቸው።

የሕዝብ ሰቆቃ ከቤተ መንግሥት ሆነው ታያቸው፡፡ ከመንግሥት ሹመት የህሊና ሹመት በእጅጉ እንደሚበልጥ አምነው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲቀላቀሉ በአዋጅ የሚያገኙትን የቀድሞ ፕሬዚደንት መብትና ጥቅሞች ተነጠቁ አሁን መኪና ስሌላቸው በታክሲ እየተጠቀሙ ነው፡፡

በ40 ዓመት የፖለቲካ ትግላቸው የጠበቁትን የሁሉም የሆነችውን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ስለአላስገኘላቸው ትግላቸው በግል በተወካዮች ም/ቤት እና መድረክን በመፍጠር ቀጥለውበታል፡፡ ብሔር ብሔረሰቦችም ሆኑ በአጠቃላዩ የኢትዮጲያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያገኝ ከፍተኛ መስዋትነት እየከፈሉ ናቸው፡፡ በዛሬው ተሪካዊ ቀን ደግሞ ትግላቸውን በተደራጀ አካሄድ ለመቀጠል የአንድነትን ፓርቲ በሙሉ ፍላጎታቸው ተቀላቅለዋል፡፡ አንድነትም እንኳን! እንኳን! ደህና መጥሉልን በማለት የፈጠሩትን መድረክ አብረን እናጠናክር የሚለውን መልእክት ለእርሶዎ በአክብሮት አስተላልፋለሁ፡፡

አቶ ስዬ አብርሃ የደርግን ኢ-ዴሞክራሲያዊ ኢ-ፍትሐዊ አገዛዝ የአስወገደውን የኢህአዴግ ጦር የመሩ ሲሆን ይህንኑ ወታደራዊ ችሎታቸውን በመጠቀም የኤርትራን ወራሪ ጦር በመደምሰስና በማባረር የአገራችንን ሉዓላዊነት የአስከበሩ ብርቅዬ ዜጋ ናቸው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ በግንባር ቀደም ከሚፈልጓቸው በጣት ከሚቆጠሩ የዱሮ የትግል አጋሮቻቸው የመጀመሪያው ሊሆኑ ሲችሉና በዚህም በሚያገኙት ከፍተኛ ሥልጣን የላቀ ምቾት ያለው ሕይወት መምራት ሲችሉ በኢትዮጱያ የሉዓላዊነት አጠባበቅ ላይ በመርህ በመለያየታቸው ለ6 ዓመት በእምነታቸውና የኢትዮጱያዊ አቋማቸው ለስር ተዳርገዋል፡፡

በዚህም ክቡር አቶ ስዬ አብርሃ የስልጣን ሳይሆን የእምነት ሰው መሆናቸውን በተግባር አረጋግጠዋል፡፡ አቶ ስዬ አብርሃ ለሕግ የበላይነት፣ ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለብሔር ብሔረሰቦች እኩልነትና በአጠቃላይ ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጱያ በርካታ ታጋዬችና ወጣቶች እንደተሰው ግንባር ቀደም ምስክር ናቸው፡፡ ይህ ግዙፍ መስዋትነት የተጠበቀውን ዴሞክራሲያዊ ውጤት ባለማስገኘቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአፈና አገዛዝ በኢህአዴግ መንግሥት መቀጠሉን ተገንዝበናል፡፡ አቶ ስዬ አብርሃ ከዚህም እውነተኛ ግንዛቤ በመነሳት ነው፡፡ ከኢህአዴግ ተለይተው ቀጣይ የዴሞክራሲ ትግል እያካሄዱና እያስተባበሩ የአሉት፡፡

አቶ ስዬ አብርሃና የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የተያዩት በአራዳ ፍ/ቤት ብርቱካን በዳኝነት በተሰየመችበት ጊዜ ነበር፡፡ የመንግሥትን ተጽእኖ ተቋቁማና የዳኝነትን ነፃነት በተግባር በመፈፀም አቶ ስዬ አብርሃ የዋስ መብት እንዲያገኙ ወስነች፡፡ በዚህም ውሳኔ ምክንያት በሕገ መንግሥቱ የተሰጠው የዜጎች የዋስትና መብት የስዬ አዋጅ እየተባለ በሚጠራው የ24 ሰዓት ድንጋጌ በተወካዮች ም/በት እንዲወጣ የተደረገውና በማረሚያ ቤት ለበርካታ ዓመታት የታገሉለትም፡፡
የሕግ የበላይነት በመጥፋት የሠላማዊና ደሞክራሲያዊ ትግል እንዲያካሂዱ መንስኤ ሆኖአቸዋል፡፡ አቶ ስዬ የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የልማት ችግሮች በዘለቄታው የሚፈቱት በተቃዋሚ ፓርቲዎች ትብብር ብቻ መሆኑን ስለማያምኑ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ የአንድነት መድረክ እንዲፈጠርና እንዲጎለብት ከፍተኛ አስተዋጽአ አድርገዋል፡፡ አሁን ደግሞ በዛሬው ቀን የአንድነትን ፓርቲ በመቀላቀል፡፡ በመድረክ የጀመሩትን የፓርቲዎችን የማጠናከር ሥራ በገሃድ ጀምረውታል፡፡ እኛም አንድነቶች አቶ ስዬ አብርሃን እንኳን! እንኳን! መጡልን በማለት የተሰማንን ከፍተኛ ደስታ እንገልፃለን፡፡

የአንድነት ፓርቲ ዛሬ ከምንግዚውመ በላይ ጥንካሬ የአገኘበት ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ የዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና የአቶ ስዬ አብርሃ አንድነትን መቀላቀል የአንድነት ፓርቲ የሁሉም ኢትዮጵያውያኖች የዴሞክራሲ ቤት መሆኑን ከማብሰሩም በላይ ቤቱን ያሻሽሉታል፣ ያጠናክሩታል ብለን እናምናለን ቤት ለእንቦሳ ስትሉን፣ እምቦሳ እሰሩበት፣ ዴሞክራሲን አዳበሩበት፣ በቤቱ ሁሉም ኢትዮጱያውያኖችን በእኩልነት አበልጽጉበት እንላችኂለን፡፡

ይህንንም ከእናንተ ጋር በማድረጋችን የኢትዮጱያ ፖለቲካ ላንድእስኬፕ (Political Landscape) በእጅጉ ይለወጣል፡፡ የኢትዮጱያ ሕዝብ ተስፋ ይለመልማል፡፡ በዚህም የበርካታ ኢትዮጵያኖች ብሔር ብሔረሰቦች አበሮ በአንድነት የመታገለ መንፈስ ተጠናክሮ ፍትሕና እኩልነት የሰፈነባትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በነፃነት ፍትሐዊ ምርጫ በቅርብ ጊዜ ለማየት ይኖርበታል፡፡ ይህ የእኛ ትውልድ የዜግነት ግዴታ ነው፡፡ ይቻላል! እናደርገዋልን፡፡

ከዚህ ታሪካዊ ውሳኔና ዝግጅት ሊመድረስ አመራሮች መዋቅራዊ ቡድኖች በርካታ ዜጎች የአለሳለሰ ጥረት በማድረጋቸው ፓርቲው ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል፡፡ ከእነዚህ መካከል የተወሰኑ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በወጣት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ለተደራጁት አባሎቻችን የላቀ ምስጋና ይድረሳችሁ እላለሁ፡፡

የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ አስቻለው ከተማና ጓደኞቹ የዚህ መስተንግዶን (Reception) ሙሉ ወጭ በመሸፈናቸውና ስፖንሰር በማድረጋቸው የአንድነት ፓርቲ በዚህ ታሪካዊ ቀን ታሪካዊ የሆነ ምስጋና ያቀርብላቸዋል፡፡

ውድ ወዳጆቻችን፡- የኢትዮ-ቻናል ጋዜጣ በትላንትና እትሙ ላይ ለአለን የገንዘብ ችግር ተጨንቆ ለዝግጅቱ ከፍተኛ ገንዘብ መፍሰሱን ዘግቧል፡፡ አቶ አስቻለውና ጓጆቹ ይህንን ወጭ መሸፈናቸውንና ፓርቲውን ከወጭው ማዳናቸውን በቅዳሜ እትሙ እንዲገልጽልን አሳስበዋለሁ፡፡

አመሰግናለሁ

ኢ/ር ግዛቸዉ ሽፈራዉ

ም/ሊቀመንበር